# *የታሪክ ብረዛ-- ለወኔ አይጣፍጥ፤ ለአዕምሮ አይጥም*

***ሀማ ቱማ***

***ያልነበረ ያርዳ የተባለ ይመስል***
***ያልነበረ ያውራ የተባለ ይመስል***
***የእነ ነበርን ወሬ ሀገሪቷን ሞላት***
***የነበረው ሳይሆን ያልነበረው በላት፡፡***

***ያልነበረ ያፈርሳል የተባለው ቀርቶ መከራችን ሆኖ የነበሩት ማፍረስን ተያይዘው ታሪክን ሲበርዙና ሲያፋልሱ መመልከት በምግብ ፈንታ ቁርስ ምሳ ሆኖብናል፡፡ ወደ ኋላ ዞራችሁ ታሪክን አትቆ የሚሉን ብቅ ማለታቸው ምስጢር አይደለም፡፡ ይህን ባዮቹ ግን ትላንትን ሳይሆን የዛሬ መቶ ዓመቱን-- ያውም በሀሰት-- እየጠቀሱ ለም መሬታችንና የዱር አራዊታችን በወራሪ አማራ ተበዘበዘ-- ጠፋ ብለው ወጣቶችን በተለይም አርሶ አደሮችን በሀሰት ታሪክ በርዘው ለጥበትና ለጥፋት ማሰለፋቸው የሚታወቅ ነው፡፡ ወያኔና መሰሎቹ ከተመሰረቱ ጀምሮ የሕዝብን ዕይታ ወደ ኋላ ኋላ እየጎተቱ በማንሸዋረር ጥላቻን አራግበው መጓዛቸው የሚታወቅ ሀቅ ሆኖ ሳለ ዛሬ ወያኔነታቸውን ሳይሆን ከመለስ ጓደኝነታቸውን ሰረዝን የሚሉን ግለሰቦች ትላንት ለፈፀሙት ወንጀል ከሕዝብ ይቅርታ መጠየቁ የማይችሉት ሸክም ሆኖባቸው ያለፈውን እርሱት ይሉናል፡፡ ሌሎች ደግሞ ያለፈው ከተነሳማ ወንጀለኛ ሁሉ ከወያኔ ጎራ አይከጻምና ዝም እንበላቸው ሲሉ ይማፀናሉ፡፡ ታሪኩን የረሳ ስህተቱን ይደግማል ከመሆኑ ሌላ የወላጅ ገዳይን አባዬ እማዬ ብሎ መሳምንም ሊያስከትል ይችላልና  ታሪክን እርሱ የሚለው ሰበካ  ከቶም አይበጅም፡፡***

***ይህ እንደ መግቢያ ይሁንና ታሪክ አይበረዝ የሚለውን መፈክር ዳግም ማስተጋባት ግድ ሆኖ የሚገኘው በታሪክ ብረዛ የተጠቃውን የፈረደበትን ድርጅት ማለትም ኢሕአፓን ለመከላከል ብቻ ሳይሆን  ታሪካችንን ካልጠበቅን ትግላችንም ሊደናቀፍና ለረጅም ጊዜ ለወያኔ ተገዢ ሆነን ልንቆይ ስለምንችል ነው፡፡ ታሪክን ማስታወስ፤ ሀሰት ሀቅን እንዳያፍን ነቅቶ መከላከል ስንልም ቂምን እንደ ፅጌረዳ ተክል ውሀ እያጠጣን እናቆይ ለማለት አለመሆኑ ግልፅ ነው፡፡ መርሳት ሌላ ይቅር ማለት ሌላ እንዲሉ፡፡ ታሪካችንን መለስ ብለን ስናይ ሕዝባችን ያለፈበት ሂደት ከነበረው ጊዜና ዕድገት ደረጃ ጋር ተዛምዶ መገምገም ያለበት መሆኑ መካድ የለበትም፡፡ አፄ ቴድሮስን ወይም አፄ ምኒሊክን በዛሬ መነፅር አይቶ ለማውገዝ መነሳት ትክክል አይደለም ስንል ደጋግመን አሳስበናል--በተለይም ገምጋሚና ወቃሾቹ ራሳቸው ዛሬ ባለንበት ምዕተ ዓመት የዱሮ ጨለንቆ ያሉትን በአሶሳና በደኖ እያጀቡና በአርባጉጉ እያደመቁ እያየናቸው! ከዚያም ሌላ ባልሆነና ባልተሰራ መሰረት ክስ ሲቀርብ ደግሞ አግባብ አይሆንም ማለት ይቻላል፡፡ ወያኔ ለአባላቱ ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ ሲያቀርብ የነበረው ሀሰት በሬ ወለደ እንደነበር ሰምተናል፡፡ ዛሬ  ከነወንጀሌ ንስሐ ባልገባም ኢየሱስ ተቀበለኝ ብሎ የሚቀባጥረው ታምራት ላይኔም ኢሕዴን ብሎ በወያኔ ታቅፎ ሲቧርቅ በሻዕቢያ የሜዳ ራዲዮ በአፄ ምኒሊክና በጀግናው አሉላ አባ ነጋ ላይ ሲያወርድ***

የነበረውን አሳፋሪና ውሸት አዘል ውርጅብኝ ዛሬም የምንረሳው አይደለም። (በወያኔ ወንጀሎችም ቀጥተኛ ተባባሪ ሆኖ ሳለ አሌ ብሎ ይክዳል፤ ገንዘብ መስረቁ የአደባባይ ምስጢር ሆኖ እያለ ዓይኑን በጨው አጥቦ ይክዳል። ድንቄም ህይማኖት!) በኢትዮጵያ ወይ በፈረደበት አማራ ቅኝ ተገዛን ወይም አሁንም በዚህ መንገድ እየተገዛን ነው የሚሉትም ከታሪክ መጣላታቸው ግልፅ ነው ። የተሳሳተ ዓላማና ተልዕኮን ከግብ ለማድረስ ታሪክን ማዛባቱና መበረዙ ለሚመለከታቸው አስፈ ላጊ ነው። ወያኔ የኢትዮጵያን ህልውና ለመሸርሸርና ሕዝብን ለመከፋፈል የሕዝብን ታሪክ መበረ ዙ ያስፈልገዋል። ሀቅን ተናግሮ ሊከፋፍል ስለማይችል አዲስ የሀሰት ታሪክ መፍጠር ነበረበት፤ በአሁኑ ጊዜም ሳይታክት ይበርዛል፤ ይከልሳል። ግራዚያኒ መንግሥቱ በጊዜው ኢሕአፓን ከሕዝ ብ ለመነጠል ሀሰት በሀሰት ከምሮ ድርጅቱን በመወንጀልና በመክሰስ የነዛው ሁሉ ዛሬም በአንዳን ዶች እየተስተጋባ መሆኑ ይደመጣል። ውሸት ሲደጋገም እውነት ይመስላል ያለው የሂትለር የፕሮፓጋንዳ ሀላፊ (እሱም ዶክተር ነበር!) ደቀ መዝሙሮች ዛሬ ብዙ ናቸው። በተለይ በአማራ ው ሕዝብ ላይ ጠባቦች በየፊናቸው የረጩት የሀሰት ቅስቀሳ በአያሌ ፈረንጆች አሁንም እየተስተ ጋባ ነው። መጥፎ ወሬ ይበራል፤ መልካሙ ይተኛል ብለዋል ወላጆቻችን። መልካሙ ከተኛ ግን እስኪነቃ ሀገርን መቀማት ሊከተል ይችላል።

ታሪኩን የረሳ ቅርሱን የዘነጋ
የሞተለትንም ያልሰጠ ምስጋና
ጠላት ይገዛዋል ባሪያ አርጎ ቀጥቅጦ
ማን ሊያዝንለት ይሆን እሱ ራሱን ጥሎ ።

ስለዚህም ታሪክ አይበረዝ ስንል ሀገርን የመከላከል እርምጃ መሆኑ መታወቅ አለበት። ታሪክ አይበረዝ ብለን ስንነሳ ደግሞ አንዳንዶች ጥላቻ ነዛችሁ፤ ምሁሮችን ዘለፋችሁ፤ ታዋቂ እገሌን ደፈራችሁ ብለው በመወንጀል ብዕራችሁ ይንጠፍ ጉሮሮአችሁ ይዘጋ፤ ምላሳችሁም ይታጠፍ ይሉናል። ከእምባጮ ለሰሩት ታቦት ይሁን ጣዖት ሁሉ ስገዱ ባይ ናቸው። ታሪክ ሲበረዝና በደም የተገኘ ቅርስ ከትቢያ ሲጣል ዝም በሉ መቸም ማንም ንቁ ዜጋ ሊቀበለው የሚችል ግሳፄ ወይም ምክር ሊሆን አይችልም። በተለይ በአሁኑ ጊዜ ወግ አጥባቂ ነን በሚል ሽፋን፤ ኢትዮጵያዊ ነን በሚል ጭምብል የትውልድን ተጋድሎ ሊያደባዩና የመጪውንም የትግል ይዘትና አቅጣጫ ሊያስቱ የተነሱ በዝተው እያለ ። ከሁሉ በፊት ግን ምሁር ስንል በሆነ የፈረንጅ ትምህርት ቤት ፊደል ቆጥሮ፤ ዓመታት ቆጥሮ ታርጋ የተለጠፈበትን ወይም የምስክር ወረቀት የተቀበለውን ማለታችን እንዳልሆነ መታወቅ አለበት። መማር ራሱ አጉል ጥንቆላ ከመሆን ላያልፍ እንደሚች ል መለስም ባልዲግሪ ነውና ያየነው ነው። መማር ለጠባቦች መንጋ በሎሌነት አድሮ፤ በወገን በሀገር ላይ መጨከን ከሆነ --
ይቅርብኝ ልደንቁር ይቅር ባልማረው
ተማረ የተባለው ሰው መሆን ካቃተው

የተባለውን እንድንደግም ይጠይቀናል። ምሁር ስንል

አዋቂ ከሆነ አዋቂነት ደግሞ ቢያንስ ሀቀኝነትን ማጠቃለል አለበት። ለሆድ ሳይሆን ለሀገር ጥቅም ቅድሚያ መስጠት፣ ሀቅንም በተመለከተ ደፋር መሆን፣ ሀገር ወዳድ መሆን፣ሐዋርያ አርአያ መሆንን ይጠይቃል። በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ምሁር የምንለው የጋን መብራቱንና ከትግል ርቆ ውሀ ገብቶ (ያውም አባይ ሳይሆን የዋሺንግተኑ ፖቶማክ ውስጥ) የሚያልበውን ሳይሆን የሀገርና የሕዝበን ሰቆቃ ሰምቶ አለሁላችሁ የሚለውን ነው። ስንቱ አዋቂ ኢትዮጵያዊ አራሽ ሆኖ፣ ባዕድ ሀገር ታክሲ ነጂ ዘበኛ ሆኖ፣ በኢትዮጵያ አንገቱን ደፍቶ እየኖረ መሆኑን እናውቃለን። አንድ ጀግና ትወልድ ለሀገር ብሎ ሲዋደቅና መስዋዕትነት ሲከፍል በቦታው ያልተ ገኙ ዛሬ ተመልሰው ያንን ትውልድ ሊቀጠቅጡ ዘመቻ ሲከፍቱ በዝምታ ልናልፍ አይጠበቅም። ስለዚህም ሁሉን--በተለይም ቀንደኛውንና መድረክ አጣባቢውን-- በየስሙ ከነታሪኩ ጠቅሶ-- አትዋሽ፣ ታሪክን አትበረዝ፣ የሕዝብን ቅርስ አታቆሽሽ ማለት አለብን። ይህ የሚያስቆጣቸውና ቅር የሚያሰኛቸው ካሉ ይቅርታ ልንጠይቃቸው ባይጠብቁ ይሻላቸዋል።

ዛሬ ባህላችን ለባርነት አመቻቸን ብለው በደፈናው በድፍረት የሚናገሩት ፕሮፌሰር መስፍን ለምሳሌ የዚሁ የብረዛ ዘመቻ ዋነኛ አቀንቃኝ ሆነው ቆይተዋል። ለረጅም ጊዜ በአክብሮት ብንይዛቸውም ለ "ታገል" የተማሪዎች ጋዜጣ አማካሪ አልሆንም ብለው ያኔ ጥንት ካስገረሙን ጊዜ ጀምሮ፣ የአሜሪካንን ፖለቲካ ደግፈው ክርክር ከገጠሙን ከያኔ ያኔ ጀምሮ፣ ደርግን ስልጣን ለሲቪል አትልቀቅ ብለው ካስጠነቀቁና ጠመንጃው በእጅህ ነው ብለው መከሩ ከተባለ ጊዜ ጀምሮ፣የሽማግሌ መንግስት በሚል ፈሊጥ ደርግን በመጨረሻ ለወያኔ ለማዳከምና ለማመቻቸት የተጫወቱትን ሚና ስናጤን፣ እነ ፕሮፌሰር አስራት ለግንጠላ እጅ አንሰጥም ብለው ፀንተው ሲቆሙ እሳቸው ከመለስ ዜናዊ ጋር ተሞዳሙደው፣ ልጆቼ ወዘተብለው መክረው፣ኢደኃቅን ደም የጠማው ብለው አውግዘው፣ ኢሕአፓ በነጭ ሽብር ለፍርድ ይቅረብ ብለው፣ በወያኔ ተይዘው የጠፉትን የኢሕአፓ መሪዎችና አባሎች ጉዳይ ባነሳ መብረቅ ይምታኝ ብለው፣በሰላማዊ ትግል አባወራነት ሽፋን ፀረ ወያኔውን የትጥቅ ትግል ሙከራ ሁሉ አውግዘው፣ ቅንጅትን በመከፋፈል ሚናቸውን ተጫውተው፣ወዘተ ያደረሱትን ተከታታይ ጉዳት ስናይና በተለይም እሳቸው ጠባይ አሳምረው ከደርግ ጋር ተቻችለው ሲኖሩ በግፍ የተረሸነውን ወጣት ትውልድ ነጋ ጠባ ሲያወግዙ ስንሰማ "አልበዛቶም" ፕሮፌሰር መስፍን፣ ዝም አይነቅዝም ዶክተር፣ በቃ ልንላቸው ይገባል። የታገለውንና እየታገለ ያለውን በማውገዝና በማጥቃት እሳቸው ወደደዱትም ጠሉትም ሚናቸው የሕዝብን ትግል ማዳከም መሆኑን መንገርና የተያያዙትን የታሪክ ብረዛ (ለባርነት ያመቻቸን ባህ ላችን ሳይሆን በቅድሚያ የእሳቸው ዓይነቱ አፍራሽ ቅስቀሳና ድርጊት ነውና) አቁሙ ማለት ተገ ቢ ነው። እሳቸው መባልን በራሳቸው ተፃረውታልና በሰልፋቸው መሰረት ሊመዘኑ ያሻል። ፕሮፌሰሩን ጣዖት ያደረጉ እዩዬን ቢያቀልጡ የምንገረም አንሆንም።

ሩቅ ሀገር ያስዋሻል እንደተባለው ሌሎችም በዚያ ትውልድ ላይ ከመዝመታቸውና ታሪክን ከመካ ዳቸው ባሻገር ዛሬም ትግሉ ቀና መንገድና መሰረት እንዳይዝ አወቅን ብለው ሎሌነትንና ውዠን ብርን ይሰብካሉ። አንድ ሰሞን ስልጡን ፖለቲካ በሚል ሽፋን ፀረ ወያኔውን ትግል በእጅ መስጠ

ት ሊፈርጁ የሞከሩ እንደነበሩ እናስታውሳለን። በዓለም አቀፍ ደረጃ በፊልም ሰሪነታቸው የታወቁት አቶ ሀይሌ ገሪማ በቅርቡ ያበረከቱት ጤዛ የሚለው ፊልማቸው በዓለም አቀፍ ደረጃ አድናቆትን ና ሽልማትን ያገኘ መሆኑ ይታወቃል። ከዚህ ተያይዞ ግን አቶ ሀይሌ የሰጧቸው ልዩ ልዩ ቃለ መጠይቆች (ለአዲስ አበባው ፎከስ መፅሔት፤ለፌስፓኮ ወዘተ..) ግን ያን የታገለውን ትውልድ በሀገር አጥፊነት የሚወነጅል ነው። ስለ ቀይ ሽብር የማውቀው የለም ቢሉም ( ስለማያውቁት የምኒሊክና ጣይቱ ፍቅር ግን ፊልም ልሰራ እፈልጋለሁ እያሉ?) ፊልማቸው ያንን የቀይ ሽብር ሰለባ የሆነውን ትውልድና ድርጅት ያክቸለችላል። ትግሉና ሽብሩ ሲካሄድ አሜሪካ የነበሩት አቶ ሀይሌ በዚህም ፊልማቸው ቢሆን የታገለው ትውልድን መስዋዕትነት ስህተት ብለው የተሳሳተ ግንዛቤን ለአዲሱ ትውልድና ለባዕዳን ያስተላልፋሉ። ፖለቲካ አልወድም፤ ፖለቲከኞች ሁሉ ውሸታሞች ናቸው፤ ፈሪ ነኝ ጠመንጃ መያዝና መተኮስ አልወድም ወዘተ በሚል መልሶችን የሰጡት አቶ ሀይሌ ገሪማ ያን ያልፈራ ትውልድ ግን የባዕድ ርዕዮትን ይዞ ኢትዮጵያን ሊያጠፋ ታገለ ብለው ያወግዛሉ። ባለፈውም ፊልማቸው ጎንደር ተጉዘው ሕዝብ-ዘመድን ሲጠይቁ ኢሕአፓ ተብሎ እገሌ ተገደለ ሲሏቸው በታች በእንገሊዝኛ ሲተረጉሙ ኢሕአፓ የተባለውን ሳይፅፉት ሲያልፉም ታዝበናል። ጭፍን ጥላቻ? ለምን? ያ ትውልድ የተሰዋው ሀገሩን ጠልቶ ነው ብሎ መዋሸት ለምንስ አስፈለገ? ሀገር ከጠላ ህይወትን ለምንስ ሰውይገብራል? ያ የኔ ብጤ ሁሉ ጥቅም አግኝቶ? ድርጅቱንና ትውልዱንም በሀሰት መክሰሱ ለምን ነው? ታሪኩን ካላወቁ ለማወቅ መጣር አይሻልም ነበር? ለራሱ አያውቅ ሰው አይጠይቅ ከመባል ያድን ነበር። አቶ ሀይሌ ገሪማ ከኢትዮጵያ አንፃር ሲገመገሙ ታሪክን የሚበርዙና ለሀቅ ተገዢ ያልሆኑ ጀግናን ወቃሽ ናቸው።

በእሳቸው ዓይነት ደግሞ በካናዳ ነዋሪና ዜጋ የሆነ ነጋ መዝለቂያ የተባለ ፀሀፊ በካናዳ መንግሥት ሽልማት ባገኘበት (ግን እሱ ሳይሆን አንዲት ፈረንጅ ፃፈችው በሚል ውዝግብ በተነሳበት) የእንግሊዘኛመፅሀፉ የሕይወት ታሪኬ ብሎ “ አደራ እንዳትስቁ” ፈጠራውን ቢያቀርብም ለለውጥ የታገለውን ትውልድ በጅምላ የምሁር ወንበዴ (ኢንቴሌክችዋል ተግስ) ብሎ ከማውገዙ ሌላ በጅጅጋ ኢሕአፓ አባል ሲመለምል አንዱ ይመጣና አባል ሁን ተብለሀል ሲል አልፈለግም ካልከው እዚያው በጥይት ይደፋሀል ሲለ ዋሽቷል። ይህ በተጨባጭ በትግል ያልተሳተፈና “ ያልፃፈውን መፅሀፍ ፃፍኩ ብሎ” ለቅሌት የተጋለጠ ግለሰብ አፄ ምኒሊክንም በጭፍን መንቀፍና ይህን ሁሉ ውሸት ማቅረብ የተገደደው (እንኳን ኢሕአፓ፤ ኢሠፓም ቢሆን አባል ካልሆንክ ብሎ በዚያው ሲረሽን አልሰማንም!) በትግሉ ጊዜ ሚናው ባዶ በመሆኑ (አማራ በምዕራብ ሶማሊያ ነፃ አውጪ ግንባር ገብቶ ታገለ የሚለውን ቀልዱን ትተን!) ሀፍረቱን ለመደበቅ ሳይሆን አይቀርም ብሎ መገመት ቢቻልም ጥፋቱ ግን በቀላሉ የሚታለፍ አይደለም። ሌላ ቅጥረኛ ፈረንጅ ፒተር ሽዋብ የተባለም ደርግን ለመደገፍ ሲነሳ በዚያ ታጋይ ትውልድና ኢሕአፓ ላይ ያሰራጨውን የፈጠራ ወሬና ክስ የምናስታውሰው ነው። የኢትዮጵያን ታሪክ በተመለከተም የኤርትራ እንቅስቀሴን ደገፍን ያሉ ባዕዳን ፀሀፊዎች (የሺንድለር ሊስት የተባለውን ታዋቂ መፅሀፍ የፃፈው ቶማስ ኪኔሊ ፤ዳን ኮኔል፤ማቹ አብዱራህማን ባቡ ወዘተ ) ፤ አነግን ደጋፊዎች እነ ፒተር ኒግሊ፤የጀርመን ቄሶች፤ሱዛን ሆልኮምብ፤ ወዘተ..) ፤ የወያኔ አፈ ቀላጤዎች ሁሉ የፃፉትና ያሰራጩት አባይ

*ደረቀ ሀሰትና የታሪክ ብረዛ በጣም ብዙና ጎጂም ነው፡፡ ለብዙዎቹ መልስ ለመስጠት በየጊዜው የሞከርን ቢሆንም ግዳጁን ተካፋዮች በማነሳቸው ስራው ገና አልተሰራም፡፡ የሀገር ታሪክ ሲካድ አሌ ብሎ ከመነሳትይልቅ በራዦቹን ማጀብና በዚያ ትውልድና በታገለው ድርጅት ላይ መዝምቱ የተመረጠ ይመስላል፡፡*

*በአሁኑ ጊዜ ታሪክን በማጣመምና በዚያ በታገለ ትውልድ ላይ በመዝመት ግንባር ቀደሙን ቦታ የያዙት በዚያው ትውልድና በኢሕአፓ ላይ ወንጀል የፈፀሙት መሆናቸው የሚታይ ነው፡፡ በአንድ በኩል ከማንም በላይ ኢትዮጵያን አፍቃሪ፣ ባህሏን ወዳጅ ሆነው በመቅረብና ጭራሹኑም ጨርቃቸውን የጣሉ ወግ አጥባቂዎች ሆነው በመለፈፍ ያ ትውልድ የባዕድ ርዕዮት አምጥቶ ሀገር ን ጎዳ፣ ፍጅት አመጣ ብለው ይከሳሉ፡፡ ያ ትውልድ የተፈጀው በአረመኔው ደርግ አገዛዝ ሆኖ ሳለ ፣እነሱም ራሳቸው የዚሁ አገዛዝ ነፍስ ገዳዮቹ ወይም ታጣቂ ካድሬዎች እንደነበሩ እየታወቀ፣ ከመ ቅፅበትም ከአፄው አገዛዝ ደጋፊነት ወደ የቀይ ቀይ ማርክሳዊ ሌኒናዊነት ተቀየርን ብለው ሲምሉ ያልተደመጡ ይመስል፣ አንዲት የንስሀ ቃል ሳያሰሙ፣ አጥፍተን ነበር ሳይሉ ያን የፈረደ በትን ትውልድ በቃልና በመፅሀፍ ይወነጅላሉ፣ በየ ድረ ገፁ ያብጠለጥላሉ፣ በፓልቶክ መድረካቸ ው ይከሳሉ፡፡ የነዚህ ዓይነቶች ታሪክ በራዦች ዋና ምሳሌ የደርግ ኢሠፓ ታጣቂ ካድሬ የነበሩት ፕሮፌሰር መሳይ ከበደ ናቸው፡፡ ስም አይጠሬ ነፍስ ገዳዮች፣ ጨካኝ ካድሬዎች፣ ነፃ እርምጃ አራማጆች ወዘተን ደግሞ ዛሬ በየብሄረሰቡ ድርጅት ሳይቀር ገብተው ቢደበቁም ሊከሱ ሲወራጩ ማንታቸውን ማጋለጣቸው አልቀረም፡፡ ዝምታም ፀፀት ነው ቢባልም እነዚህ ጉዶች በእነሱ ብሶ ከጭፍጨፋቸው የተረፈውንና አዲሱን ትውልድ በታሪክ ብረዛ ሊያቆስሉት ይጥራሉ፡፡*

*ድሮ የተማረ ለሀገር ይጠቅማል*
*ያኔ የተማረ ወገኑን ይረዳል*
*የዘንድሮ ትምህርት ግቡ ተለውጦ*
*ተምሮ ማደንቆር ሆነ አሉ ተልዕኮ ፡፡*

*ከላይኞቹ ለየት ባለ መንገድ ታሪክን እየበረዙ ያሉት ደግሞ ቀደም የፖለቲካ ታሪክ ጭራሽም የሌላቸውና ከየፈረንጁ ዩኒቨርስቲ ዲግሪ ተረክበናል በሚል ለስማቸው ቅፅል ለጥፈው አሊያም ስማቸውን ሳይቀር ፈረንጂኛ ቃና ሰጥተው ፖለቲካ ሊያስተምሩን የተነሱትና ገና ሀ ሲሉም በዚያ ትውልድ ላይ መዝመቱን የመረጡት ናቸው፡፡ እነዚህ ብዙዎቹ የሀገራቸውን ታሪክ ጠንቅቀው ያላወቁ፣ የተካሄደው ትግል ምን ይዘት እንደነበረው ያልተረዱ፣ በፀረ ወያኔው ትግል የተከፈለው ን መስዋዕትነት ሊያከብሩ ቀርቶ ሊያወግዙ የሚዳዳቸው፣ ስለ ወያኔ ማንነት ከግልብ ነባቢትና የታባቱ ባሻገር በሚገባ የማያውቁ፣ አሜሪካ ነፃ ያወጣናል እንፅልይለት እንለምነው ባዮች፣ ካለፈ ው ተመክሮ ለመማር ቅንጣትም ፍላጎት የሌላቸው፣ ሀገር ሀገር ቢሉም ፈረንጅ አምላኩ የሆነ የባዕድ ገደል ማሚቴዎችና የኔ ብጤውን፣ብዙሀኑን ሕዝብን የሚንቁ ምርጥነት የሚሰማቸው*

ግብዞች ናቸው:: ሳያውቁ የሚጠሉ ናቸውና ያን ትውልድ ማውገዙን ስራዬ ብለው ተያይዘውታል:: አዲስ የሰለጠነ ፖለቲካ ልናሰፍን ነው፣ መሀይማን ሁሉ አድምጡኝ፣ ከስሙ በፊት ማዕረግ ቅፅል ያልለጠፈ ከአፀደ መቅደሱ ይውጣ፣ ለዘለዓለም ዝም ይበል፣ ወዘተ ይሉና ፀሎትና ምለላ፣ አሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በርከክ ብሎ አድህነነ ከመዓቱ ስውረነ በምህረቱ በቡሽ (ዛሬ ደግሞ ኦባማ ሆኗል መሰል) መድህኒቱ ን እንደ መፍትሄ ያቀርባሉ:: ዝብርቅርቅ ፖለቲካቸው ከሰላማዊ ትግል እስከ ፀሎትና ጭፍን ፍቅርን ያለውን አቅፎ ጠላትን ጠላት ማለት ተስኖት ሲባዝን ለአረመኔው ወያኔ ሰለባ ሆኖ ሕዝብንም ያስጠቃል:: ታሪክን መካድ፣ በደም የተገበየውን ተመክሮ ማክቸልቸልን ትተው፣ ግብዝነትን በትሁትነት ተክተው በነበረ ፣ ያልተማረና ድሀ የሚሉትንም ሕዝብ መናቁን ትትው በነበረ ፣ አሜሪካና ባዕዳንን መለመኑን ትትው በሕዝባቸው መመካትን ተምረው በነበረ ትግላችን በተደጋጋሚ ለወያኔ ሰለባ ባልሆነ ነበር::

ተንበርክኮ ፀሎት ተነጥፎ ልመና
ለአምላክ ከሆነ እንጂ ለሰውማ አይሰራ
ጎንበስ ያሉለት ሰው ልመና የበዛበት
መርገጥ መቅበር እንጂ ማዘን አይመጣለት

የሚለውን ጎህ ሲቀድ የተረዳው ትውልድ ግን ጠላትን ታግሎ አለፈ ፣ታረክን ፃፈ እንጂ ራሱንም ሀገርንም አላዋረደም:: ማን ያውራ የነበረ ብለን ደጋግመን ላልነበሩት ግን ትረካ ለሚቀናቸው ልናሳስብ እንደሞከርነው ያ ትግል መሬት ለአራሹ ፣ ዴሞክራሲ ለሕዝብ ብሎ የተነሳው በባዕዳን ተቀስቅሶ ወይም ስርዓት አልበኝነት ተጠናውቶት ወይም ያኔ አገዛዙ ይል እንደነበረው ጃንሆይ ያበሉት " ቲማቲም፣ ዕንቁላልና ብስኩት" አጥግቦት አልነበረም:: የጋሪና ፈረሱን ቦታ የሚቀያይሩ ያ ትውልድ የባዕድ ርዕዮት በመጀመሪያ ያዘ ሲሉ ሀቁ ግን ያ ትውልድ በሀገሪቷ የነበረውን ኋላ ቀር ስርዓትና ግፉን ሲገነዘብ ላስተማረው ሕዝብ መብትና ክብር ሊታገል ከወሰነ በኋላ ነው ወደ መንገድ መሻቱ የተሰማራው:: ለባዕድ ርዕዮት ሎሌ ሆኖ " ሀገር ሊበጠብጥ" የተነሳ ሳይሆን ለብዙሀኑና ለሀገሩ በመቆርቆር አፋኙንና ብዙሀኑን ጢሰኛና ሁለተኛ ደረጃ ዜጋ አድርጎ ይበዘብዝ የነበረውን ስርዓት ሊያስወግድ የተነሳ ነበር:: ሲነሳም መሬት ለአራሹ፣ ድህነት ወንጀል አይደለም ፣አርሶ አደሩ በግብር አይወገር፣ የሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መብት ይከበር ብሎ ተነሳ እንጂ ሌላ ከሀገርና ወገን ጥቅምና ፍላጎት ጋር የተቃረነ መፈክር አንግቦ አልታገለም:: እንቅስቃሴው ድጋፍ ያገኘው፣ ኢሕአፓም የሕዝብን ድጋፍና ፍቅር ያተረፈው የሕዝብ ጥያቄ አስቀድሞና አንግቦ በመነሳቱ ነው:: በዚያን ወቅት ቀርቶ ዛሬም ቢሆን ለውጥን ፈላጊ ሀይል ስርየቱን ከአሜሪካ ሊያገኝ ይችላል የሚሉ የኢትዮጵያን ታሪክ፣ ችግርና መፍትሄን በተመለከተ በቂና ጥልቅ ግንዛቤ ያላቸው ናቸው ማለት ለእኛ ያስቸግረናል:: በመሆኑን ያ ትውልድ ሀገሩን ወዶ፣ ሕዝቡን አፍቅሮ፣እንዳዛሬዎቹ አስመሳዮች ሆዱን ሳያስቀድም፣ እንደዛሬዎቹ ፈሪ ለእናቱዎች በፍርሀቱ

ሳይሸነፍ በጀግንነት መስዋዕትነትን ተቀብሏል። እምነቱ ለሀገሩ መፍትሄ መንገድ ሆኖ አገለገለው እንጂ በተጨባጭ የምናውቀው ታሪክ ያ ትውልድ ማንንም ሆነ ምንን ከሀገሩና ከወገኑ አሳስቀደ መም ብሎ ይመስክራል።

ኢሕአፓም ቢሆን ከሀገሩ በፊት ባዕዳንን ወይም ውሱን ድርጅታዊ ጥቅምን አስቀድሞ በነበር ምናልባትም የሥልጣን ባለቤት ሆኖ  ዛሬ ሕዝብ ላይ በተፈናጠጠ ነበር። የኤርትራን ቅኝ ግዛትነ ት ተቀብሎ በነበረ ፤ ደርግ ለስልጣን ሲያባብለው እሺ ብሎ ባነዳነትን መርጦ በነበረ፤ ቻይና መንግስቱ ኃይለማርያምን ስትደግፍ ቻይናን ተከትሎ ትግሉን ቢያቆም፤ወያኔ እንዳደረገው ሁሉ ሰፊ የኢትዮጵያን መሬት የምዕራብ ሶማሊያ ነው ብሎ በመፈረም የዚያድ ባሬን ድጋፍ ቢያገኝ ኖሮ፤ ሱዳን ያዘዘውን ሁሉ እንደ ወያኔ ተቀብሎ (ድልድይ ማፍረስ፤የሱዳን ተቃዋሚዎችን አሳል ፎ መስጠት፤የሀገር ዛፍን ማስጨፍጨፍ ወዘተ) ተገኝቶ በነበር ፤ ወያኔ በአሜሪካን ትዕዛዝ ረሀብተ ኛውን ወደ ሱዳን አጓጉዞ እንዳስፈጀውና ለስንዴና ዶላር እንቀደቀየረው ሁሉ አሜሪካ ሲያዘው የሀገርንና የሕዝብን ጥቅም አሳልፎ ሰጥቶ በነበረ  ፤ የዛሬ ፖለቲከኞች እንደሚሉት “ ግትርነትን” ትቶ ብልጥ ቢሆን ኖሮ፤ ለሊቢያው ገዳፊ ኢትዮጵያ የአረብ ሀገር ናት ወደ አረብ ሊግም እናስገባ ታለን ብሎ ቃል ቢገባ ኖሮ፤ ምናልባትም ለሥልጣን በበቃ ነበር። ግን ብኩርናውን እንደ  ይሁዳ ሸጦ ለሥልጣን ቢበቃ ለሕዝብ የሚበጅ ህይል አይሆንም ነበር። ኢሕአፓ ደግሞ ለሕዝብ ስርየት ና ለ ዴሞክራሲ መስፈን እንጂ ለራሱ የግል ጥቅም ስላልታገለ የከሀዲን ምርጫ መቾም አልተቀበለም። ሀቀኛ ታሪክን ስንቃኝ ያ ትውልድም ሆነ ኢሕአፓ በየትኛውም ጊዜ ለስልጣን ሲሉ፤ ለግል ጥቅም ሲሉ፤ ፈርተወና ተርበድብደው ሀገራዊ ቃል ኪዳናቸውን አላፈረሱም። ለባዕድ ሀያል ሆነ ለሀገር ውስጥ ዕብሪተኛ አገዛዝ አላጎበደዱም። ታግለው ተሰዉ እንጂ። ይህ ነው ዋናው ሀቅ፤ የዛሬዎቹን የታሪክ በራዦች ከትላንቱ ጀግና ትውልድ የሚለየው።

ግፍ ያስችላል ሲባል ዘመኑ አለፈና
ሞት ይሻለኝ ማለት ከምላስ ጠፋና
ተጎንብሶ መጫን መወቀጥ መረገጥ
ተወዶ ታቀፈ ተመርጦ መሰንበት።

የሕዝብ አብዮት በምርጥ መኮንኖች ተቀምቶ ፋሺስታዊ ፅልመት በሀገር ላይ ሊሰፍን ቀና ቀና ሲል ኢሕአፓ ከጭቁኖች ጋር ሆኖ ሊታገል ሲነሳ ለዕብሪተኛው የመኮንኖቹ ቡድን አማካሪ፤ ደጋፊ፤ ጋሻ ጃግሬና አልፎም አራጅ ነፍስ ገዳይ የሆኑ ዛሬ ያን ትውልድን ሆነ ኢሕአፓን ሊወነጅ ሉ ሊፈቀድላቸው አይችልም። የሀገርን ጥቅም በማስቀደም ኢሕአፓ ካረዱትና ከጎዱትም ጋር ቅራኔን ወደ ጎን ትቶ በጋራ ትግል ሊሰለፍ የሞከረ ቢሆንም በሕዝብና በሀገር ላይ ወንጀል በደል የፈፀሙ ሁሉ ለትላንቱ አፀያፊ ድርጊታቸው ይቅርታ ከሕዝብ መጠየቅ  ቢቀር ተመልሰው ያን ትውልድ ማንቋሸሽና መክሰስ ሊፈቅድላቸው ከቶም አይገባም። ኢትዮጵያ ሞኝ ነሽ ተላላ ተብሏ ልና በሚል ዝምታው ቀርቶ ባንዳው ሲሾምና አርበኛው ሲክቸለቸል የቆየው የታሪክ ምፀት

ማክተም እንዳለበት መታወቅአለበት፡፡ ክህደትና ወንጀል ያዋጣል የሚል ቅርስ መተላላፍ የለበት ምና፡፡ ትውልድን የፈጀው አረመኔው አገዛዝ ሆኖ ሳለ የታገሉትን በ “ አስፈጁ” ለመክሰስ መሞከ ር ፀያፍ ነው፡፡ አንድ ሚሊዮን ኢትዮጵያዊ በፋሺስት ኢጣሊያ የተፈጀው አርበኞች ስለታገሉ ሳይሆን ፣ስላስፈጁት ሳይሆን ሙሶሊኒ ፋሽስት አረመኔ ስለነበረ ነው፡፡ ሕዝብ ለመብቱ፣ ለሀገሩ ሲታገል በአረመኔ አገዛዞች መገደሉና መጠቃቱ አይቀሬ ነው፡፡ የመስዋዕት አልባ ትግል ፕሮፌሰ ሮች ከልፈፉ ባሻገር ለዚህ ተዓምራዊ መፍትሄያቸው ግንባር ቀደም ሆነው መስዋዕት አልባ ትግልን ታግለው አላሳዩንም፡፡ በተቃራኒው ሰባካቸው ተገዙ፣ ተንበርከኩ፣ ሰልጥኑ፣ ብረት አታንሱ፣ ተንበርከኩ፣ እየተገዙ ጠባይ አሳምሮ መታገል የሚል ቅብጥርጥር ነው፡፡ 18 ዓመት ሙሉ ከወያኔ እኩል ቀለዱብን ብንል የተሳሳተ አይሆንም፡፡

ያ ትውልድ አኩሪ ታሪክን ትቶ አልፏል፡፡ ያኔም ዛሬ የሚታገለውም ኢሕአፓ የዚህ ቅርስ ነፀብራ ቅ ሆኖ አሁንም አለ ፡፡ ያ ትውልድ ከአገዛዙ ጋር በጥቅም፣ በንግድ፣ በዶሮ ርቢ፣ በፕላስቲክ ፋብሪካ፣ በሆቴል ንግድ፣ በቤት ኪራይ፣ ወዘተ የተያያዘ አልነበረም፡፡ ያ ትውልድና የዚያን ጊዜ የድርጅት መሪዎች ከሕዝብ ጎን በሁሉም መስክ የተሰለፉ ነበሩና ዕይታቸው ሕዝባዊ እንጂ ከላይ ወደታች አልነበረም፡፡ ሕዝብ ሲነሳሳ ከገዢዎች እኩል ስጋት አልገባቸውም፣ ለገዢው ክፍል ቀውጢ ቀን መጣበት ብለው ፈነደቁ እንጂ ነገሮች ከቁጥጥር ውጪ ሊሆኑ ነው ብለው ባዕዳን ማማከር አልገቡም፡፡ ሁናቴው ሲጠጥር ከፎቅ ተውርውረው ተሰዉ እንጂ፣ መርዝ ጠጥተው ሞቱ እንጂ ከአገዛዙ ለመታረቅ አማላጅ አልፈለጉም፡፡ በጠላት ላየ ተፉ እንጂ ሰፊው ሕዝብ ሊገባበት በማይችልበት ሆቴል ከሕዝብ ጠላት ጋር አብረው ውስኪ እየጠጡ ጭውውትን አልመረጡም፡፡ ኢሕአፓ ወያኔን ከ1967 ዓ/ም ጀምሮ ታገለ እንጂ አላቀፈውም፡፡ ልጁ ወገኔ አላለወም፡፡ ወያኔ ኢሕአዴግ ብሎ ጭምብል ሲያጠልቅ አጋለጠ እንጂ የትግራይ ምሽት ብሎ በዋሽንግተን ገንዘብ አምጡ ሲል ወያኔ በጠራው ሄዶ ገዳሪፍ ሱዳን የተሰራን ሰፌድ በብዙ መቶ ዶላር እየገዛ ለወያኔ ድጋፉን አልሰጠም፡፡ ከወያኔ ጋር በጎጠኝነት አልተጫጨም፣ሥልጣን አልተካ ፈለም፣ ሕዝብን በተለይም አማራውን አልዘለፈም፡፡ ማን ታገለ ? ማን ተሰዋ? ማን ሀገርን ረስቶ የግል ኑሮውን ኖረ? ማን ለወያኔ ጊዜ ይሰጠው አለ ? ወያኔ በኢሕአፓ ጓዶች፣ በሕዝብ፣ በአዲስ አበባ ተማሪዎች ደም ላይ ተረማምዶ የስልጣን ባለቤት ሲሆን ማን አጨበጨበ ? አብሮ ተደራጀ ? ማን ጠበበ ? ማን እምቢ አለ ተቃወመ? ማን በእነ ፕሮፌሰር አሥራት ላይ ፈረደ ? ማን በንፁህን ደም ከወያኔ ጋር ሆኖ ታጠበ? ማን ስንቱን ሀገር ወዳድ ገደለ፣አስገደለ ? ሂሳብ ይወራረ ድ ቢባል ሲያንስ ነው፡፡ መልስ ያሻዋል፡፡ ያለፈው አለፈ ብንል ደግሞ ባለፈው በሀገርና በወገን ላይ ወንጀልና በደል የፈፀሙ ዛሬ ዓይናቸውን በጨው አጥበው ፀንቶ የታገለውን ከሳሽ ሲሆኑ ወይም ይባስ ብለው የሕዝብን የነፃነት ትግል እኛው ጉዶቹ እንምራው ሲሉ ዝም ብሎ ማለፉ የምንችለው ሽክም ሊሆን አይገባም፡፡ ከሕዝብ መከራ ሁሌም ተጠቃሚ ሆነው የሚያሾፉ ምስጦች ን ማጋለጥ ዛሬም ነገም ሀገራዊ ግዴታ ነው፡፡ ምነዋ ተቆጣችሁ፣ ደመ መራራ ሆናችሁ ለሚሉን ምላሻችን ምነው አንቆጣ አንጤስ የፈሰሰው እኮ የሕዝብ ደም ነው፣ እየጮኸች ያለችው ውዲቷና አንዲቷ ሀገራችን ኢትዮጵያ ናት የሚል ይሆናል፡፡

*ደግመን ደጋግመን ታሪክ አይካድ፣ ያጠፉ ይቅርታ ይጠይቁ ስንል ይህ ካልሆነ ዛሬ የያዝነው ትግል ወደፊት ለመሄድ ስለማይችል ብቻ ነው:: ትላንትን ረስተን ወደነገ መሮጥ ካዋጣ ሁላችን ም ወደላፈው ዓይናችንን መመለሱን ለህገር ብለን በተውን ነበር:: ግን ይህ ትክክል አይደለም:: ታሪክ በራዦች የሚደብቁት ወይም የሚያበላሹአቸው መሰረታዊ ህቆች አሏቸው:: የኢትዮጵያን ታሪክ የሚክዱት ወያኔዎችና ጠባቦች የግንጠላና ክፍፍልን ዕቅዳቸውን ሊያፀድቁ ነው:: ትላንትን እርሱና ዛሬ ተቃዋሚ ወይም ነፃ አውጪ በሉን የሚሉን ደግሞ ወንጀላቸውን ደብቀው በአዲስ መልክ ያንኑ መከራ ሊጭኑብን ስለሚያልሙ ነው:: የወያኔን አገዛዝ በሁሉም መልኩ የደገፉና ህላፊ ተባባሪ ሆነው ወንጀል የፈፀሙ፣ ለፈሰሰው ደም ሁሉ ተጠያቂነት ያለባቸው፣ የወያኔ ቀንደ ኛ ሹመኞች፣ የአርባጉጉ በደኖ ነፍስ ገዳዮች፣ ስንቱን ንፁህ ዜጋ ደብዛውን ያጠፉና ጦርነት ሊሰሩ ብን የፎከሩብን ጠባቦች፣ለእነ ፕሮፌሰር አሥራት፣አሰፋ ማሩ፣ ለጋይም፣ለተስፋዬ ታደሰና ስንቶቹ ህይወት መጥፋት ተጠያቂዎች፣ ለአንዋር መስጊድ፣አደባባይ ኢየሱስ፣ ምስራቅ ወለጋ ሰለ ባዎች ሁሉ መጠየቅ ያለባቸው ወንጀላቸውን አምነው ሕዝብን ይቅርታ ሳይጠይቁ ከሕዘብ ጎራ መደባለቃቸውን (በማንኛውም ሀይማኖት ቢሆን) መቀበል አይቻልም:: ክርስቲያን ነኝ ባይ ግለሰ ብ ደግሞ እኛ በምናውቀው ለወንጀሉ ለጥፋቱ ንስሀ ይገባል፣ ቁንጫ፣ቅማልና ትኋን በፈላበት ገዳም ይዘጋል፣ይራባል፣ ሰውነቱን ይቀጣል እንጂ የተቃዋሚ መሪ በሉኝ ብሎ ከአዲስ አባባ አሜሪካ ሄዶ ሲቀናጣ ወይም ሰባኪ ቄስ ሆኛለሁ ብሎ የአሜሪካ ቱሪስት ሲሆን አላየንም ነበር:: ማየትም አንፈልግም:: ዋልድባና ዙቋላ በላስ ቬጋስ ተተክተዋል ካልተባለ በቀር:: ለወንጀለኛ መደበቂያ የሚሆኑ የሀይማኖት ተቋሞችና የፖለቲካ ድርጅቶችም የሚከበሩ ሊሆኑ አይችሉም::*

*ትግላችን አግባብ ያለው አቅጣጫን ይዞ እንዲጓዝ ከተፈለገ በፈሪዎች ሊመራ አይችልም:: ፈሪ አይኑር የሚል መፈክር ማጮኹ ስህተት ቢሆንም ቡከን የታጋይ ድርጅት መሪ ሊሆን አይችልም ፣አይገባውም:: ፈሪ ተለይ ነጋሪት መደለቅ አለበት:: ትግላችን ድልን ሊቀዳጅ የሚችለው በወንጀ ለኞችና ያለውን ስርዓት ባዲስ መልክ ሊቀጥሉ በሚመኙ ሲመራም አይደለም:: ነፍሰ ገዳዮችና ወንጀለኞች ንስሀ ሳይገቡ በሽፍንፍን ዛሬ የትግል አባወራ ሊሆኑ ከተነሱ ያለፈው ብሶ ይቀጥላል እንጂ ለውጥ አይመጣም:: ወንጀለኛ ወግድ ተለይ ጥሩምባ ይነፋ! ታሪክ አይበረዝ ስንል በራዦ ች በግርግር የበላይነትን ይዘው መከራችን ቀጣይ እንዳይሆን በሚል ነው:: ያ የታገለውና አኩሪ ታሪክ ዕፎ ባለፈው ትውልድ ላይ ጭፍን ዘመቻ የከፈቱት ሁሉ ለህገር የሚበጅ ስምሪት አልተያ ያዙም:: የቆሸሸ ታሪካቸውን በንስሃ እንዲያፀዱ መጠየቅ አለባቸው:: ይህን ማለት ቂም አይደለም --- የገለማውን አገዛዝ ስንታገልና ለመታገል ራሳችንም መፅዳት ስላለብን ነው:: አለበለዚያ የጠገበውን ቀበሮ በተራብ ጅብ ለመተካት መጣሩ የሚጠቅመን አይሆንም::*

*በአቅዋማቸው ፀንተው ለህገርና ለወገን ብለው ህይወታቸውን የሰጡትን የምናከብረው ከህዲዎች ን በማግለልና በማራቅ ብቻ ነው:: ወያኔን እምቢኝ ብለው ህይወታቸውን የሰጡትን ፕሮፌሰር አስራትን የምናከብር ከሆነ ከደርግም ከወያኔ ያደሩትን ሌላ ፕሮፌሰር ማክበር አንችልም::*

ለሀገር ብሎ ከፍተኛ መስዋዕትነትን የከፈለ ትውልድንና ኢሕአፓንም እያወገዘን ትላንት ከወያኔ ጋር ሆነው ሀገራችንን ያጠፉትን መሪ ብለን ልናቅፍ ከተነሳን አሳዛኝ ዜጎች መባላችንና መሆናችንም የሚቀር አይደለም። ታሪካችንን ከበራዦች ነቅትን መጠበቅ ያለብን የነገ ድላችን ዋስትናና መሰረት ስለሆነ ነው። ታሪኩን የረሳ ስህተቱን ይደግማል። መስዋዕት የሆነ ዜጋን የዘነጋ ሀገር ሻጭ ባንዳውን ያወድሳል። ለዚህም ነው ከረረ መረረ ፤ ዝም በሉ፤ ያለፈው ይረሳ፤ ስልጡን ፖለቲካ፤ አዲስ ቅኝት ወዘተ የሚሉት ሁሉ አንደበታቸንን ሳይዘጉን ታሪክ አይበረዝ፤ ጀግናም አይረሳ፤ ባንዳም አርበኛ አይባል፤ ወንጀለኛም ንስሐ ሳይገባ ከሕዝብ ጎራ አይደባለቅ፤ባንዳና አንጃ ይገለል፤ የታገለውና የተሰዋውም ትውልድ ታሪክ አይካድ የምንለው።
ለዚህም ነው ለሁሉም ታሪክ ላይ ቀላጆች፤

ሌባ ጣት ቀስረው በሀሰት የከሰሱ
ለሀቅ የቆሙትን በውሸት ያጠቁ
ሌሊቱ ሲነጋ ሁሉም ተጋለጡ
በባዕድ መዲና አልቻሉም ሊጠፉ
የሀሳዊ መሲህ ታሪክ ሁሌም ክፉ

የምንላቸው።

(ግጥሞች የተወሰዱት ከ "ሀበሺኛ" ቁጥር 1 ነው)